

# የመበለቲቱ ስጦታ

ቤተ መቅደሱ ትልቅና እጅግ ያማረ ነበር። ብዙ ሰዎች እግዚአብሔርን ለማምለክ ወደዚያ ይመጡ ነበር። በቤተ መቀደስ ውስጥም የገንዘብ ማስቀመጫ ትልልቅ ሳጥኖች ተቀምጠው ነበር። ብዙ ሰዎች ገንዘባቸውን በሳጥኖቹ ውስጥ ይከቱ ነበር። በዚያ የሚጠራቀመው ገንዘብም እግዚአብሔርን ለማምለክና ለሌሎች የቤተ መቅደስ አገልግሎቶች ይውላል።

. ከእለታት አንድ ቀን ኢየሱስ ሳጥኑ ባለበት አካባቢ ተቀምጦ ሰዎች በሳጥኑ ውስጥ የሚያስቀምጡትን ገንዘብ ይታዘብ ነበር። ብዙ ሀብታም የሆኑ ሰዎች በርከት ያለ ገንዘብ በሳጥኑ ውስጥ ይጨምሩ ነበር። ከዚያም አንዲት ድሃ መበለት ሴት ወደሳጥኑ ተጠጋች።

ሁለት ትንንሽ የመዳብ ሳንቲሞችንም በሳጥኑ ውስጥ ጨመረች።

ኢየሱስም ደቀመዛሙርቱን "ይህች ሴት ከሀብታሞቹ ሰዎች ይልቅ እጅግ አብልጣ ሰጠች" አላቸው። ኢየሱስ ይህ ለምን እንደሆነ ሲያስረዳ "ሀብታሞች ከሰጡ በኋላ ብዙ ገንዘብ ይተርፋቸዋል። እነርሱ የሰጡት ካላቸው እጅግ በጣም ትንሹን ነው። መበለቲቱ ግን ***ያላትን ሁሉ*** ሰጠች።" አለ።

*የመበለቲቷ ስጦታ ታሪክ የሚገኘው በማርቆስ ወንጌል በምዕራፍ 12፡41 – 43 ባለው ክፍል ውስጥ ነው።*

http://gardenofpraise.com